# ሺ ፈረስ ከኋላ – ሺ ፈረስ ከፊቱ

ከድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ

ሺ ፈረስ ከኋላ
ሺ ፈረስ ከፊቱ
ሃገርን ሊያዋህድ
ንጉሥ ሠራዊቱ
ታላቋ ኢትዮጵያ
የነበር ምኞቱ
ይህን ሳታይ ሞተች
ዋ ያቺ እናቱ!*

ሺ ክላሽ ከኋላ
ሺ ክላሽ ከፊቱ
ሃገር ሲያፈራርስ
ምሎ ክህደቱ
በጎጥ ሲበልታት
ለቅሶዋን ምድሪቱ
ይህን ጉድ ስትሰማ
ምን ትበል እናቱ?

ዘጋቢ ፀኀፍቱ
ሊቀ ሊቃውንቱ
የድብቅ የስውር
ሴራን እየመቱ
መረጃ አከማችተው
በዓለም ሊሟገቱ
ወገንም ወዳጅም
አብረው ሊቃትቱ
እነሆ እንደገና
ተነሱ ዘመቱ

…ከጥንት ከጠዋቱ
መሬት ድንበራችን
የአገራችን ታሪክ
ቅርስ ንብረታችን
በደምና በአጥንት
የኖረ አጥራችን
ይከበር መቃብሩ
ስለእትብታችን…

የክልሉ ድንበር
እትብት ምልክቱ
ዜጋው ተወላጁ
ሲያውቀው ከጠዋቱ
ወገን ሲረባረብ
ለአገር ለመሬቱ
ክህደቱ አቅራራ
ተረት አትተርቱ
የአገር ድንበር ወሬ
አሉባልታ ከንቱ
የኢትዮጵያው የሱዳን
የባዕድ ነው መሬቱ
ቋራና አርማጨሆ
ቅኝ ነው ግዛቱ
ታሪክ ለማዛባት
አይዳዳ አንደበቱ
የባዕዱ ቀላጤ
በዛብን ክፋቱ
ሞልቶ ተትረፍርፏል
ስድብና ንቀቱ
ትንሽ አረማሞ
አዬ በጉልበቱ
መንቀል ግድ ብሏል
በርቱ ተበራቱ

ወገን ከዘብጥያ
በባዕድ ቢማቅቅም
ጨርቅ ባንዲራ ሊሆን
ብዙም ባያጓጓም
የአገር ፍቅር ስሜት
በመርፌም ባይገባም
እንግዴ ልጅ ላያድግ
ብዙ አንማፀንም
ለታሪክ ከሃዲ
ታሪክን አንጠራም
“ታሪክ ይፍረድ” ይቅር
በቃን አንፅናናም

ታሪክስ አይፈርድም
ታሪክ ሸማግሌ
መተማም አድዋም
የትናንት ምሳሌ
ዛሬን ብቻ ለሚያውቅ
የባዕዳን ሎሌ
ሺ ፈረስ ተጭኖ
ይዘፈን ውጫሌ
ክላሽም አልፈልግ
አለልኝ ሽመሌ
ለአገር ብሎ መውደቅ
መች ለቆኝ አመሌ

የክህደት የቅጥፈት
የውርደት ምሳሌ
ብልጣብልጥ ቀልማዳ
የሰው አልባሌ
የሁሉንም እናት
ያምሳት አለሌ
የናት ሆድ ዥጉርጉር
የአገር ጉራማይሌ
ጠላት ገዥሽ ሊሆን
የወደድሽ ባተሌ
ጠይቀሽ ታውቂያለሽ
"ምን ይሆን በደሌ?"

***** * ***** * ***** * *****

**እዚህ አንቀጽ ውስጥ ከላይና ከታች ያሉት ሁለት ስንኞች በከፊል እና በቁንጽል ለአፄ ቴዎድሮስ ከተገጠሙ ግጥሞች ከክቡር አቶ ተክለፃድቅ መኩሪያ የኢትዮጵያ ታሪክ መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው።*

© ድሚልኝ ብዕሬ—ዘአዲሱ ገበያ
ግንቦት ፳፻
zeaddisu_gebeya@yahoo.com
May 2008